# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 11 ቀን 19.2.67

## የማይዘነጋ ፋሽስታዊ ድርጊት

ደም አናፈስስም የሚሉት በላብአደሩ ደም ተበከሉ:: የሰፊው ሕዝብ ወገን ነን የሚሉት ስራ ስራ እያለ የሚጮኸውን ከርታታ በጥይት ቆሉት፣ በሰደፍ ቀጠቀጡት:: ፋሽስትነታቸውን በገሃዱ አስመሰከሩ:: ጥቅምት 16 ቀን በሺ የሚቆጠሩ ስራአጦች በተሰበሰቡበት በኢሰአማ በር ላይ የሚያስቀጣ ፋሽስታዊ ድርጊት ተፈፀመ፣ የብዙ ስራአጦች ደም ፈሰሰ፣ ብዙ ስራአጦች በደርጉ ቡችሎች ተደበደቡ፣ በፋሽስቶቹ ጥይት ተመትቶ ወዲያውኑ የሞተ የአንድ ከርታታ ስራ ፈላጊ ሬሳ ብቻ እዚያው እወደቀበት ስፍራ ሲቀር የቀረ፡ በሙሉ ወዲያውኑ ስለተወሰዱ ስንት እንደሞቱና ስንት እንደቆሰለ እስካሁን በትክክል ማወቅ አልቻልንም::በማወናበጃ መሳሪያዎቹ ደርጉ የሰጠው ቁጥር ግን ከእውነተኛው የራቀ መሆኑ አያጠራጥርም፣ እዚያው የነበሩት፡ከጥይት የተረፉት የአይን ምስክሮች ግን ወዲያው የሞቱት ከሰባት እንደማያንሱ ያረጋግጣሉ::

የጥቅምት 16ቱ ፋሽስታዊ ድርጊት ለምን አስፈለገ. በደርጉ የለመና መሳሪያና ጉርሻ በለመዱ ጥቂት ፀረሕዝብ ወታደሮች ህይወታቸው የጠፋው፡ደማቸው የፈሰሰውና በጠመንጃ ሰደፍ የተወገሩት ስራአጦች ኢትዮጵያ ትቅደምን የሚደግፉ ንፁህ ኢትዮጵያውያን ነበሩ፣ በሃይለስላሴ መንግስትና በባእዱ ከበርቴዎች አመጽ ከየስራቸው የተባረሩ፡የሚልሱት የሚቀምሱት ያጡ፡ከነሙሉ ቤተሰባቸው በችጋር አለንጋ የሚገረፉ፡መሰረታዊ መብቶቻቸው ተከብረው የሰፊውን ሕዝብ ኢትዮጵያ በስራ ለማስቀደም የሚጓጉና የሚጥሩ ሰዎች ነበሩ:: ታዲያ እነዚህ ስራአጥ ኢትዮጵያውያን ስራ ስራ ስላሉ በማንስ ላይ ቢሆን ምን የሰሩት በደል አለ? የማንንስ መብት ነክተዋል? ስራ ይሰጠንና እንስራ ማለትስ ምኑ ላይ ነው ህገወጥነቱ? ያለፈቃድ ተሰበሰቡ....በፀጥታ አስከባሪዎች ላይ ድንጋይ ወረወሩ..ወዘተ. የተባለው ፍፁም ሃሰት ማወናበጃ ነው:: የሰበሰባቸው አላማ ስራ ስለማግኘት ጉዳይ ለመነጋገርና ደርጉ የሚሰጣቸውን መልስ ለመስማት ሲሆን ፍፁም ፀጥታ የተመላበት ነበር:: ድንጋይ ወርውረዋል የተባለውም ፍፁም ሃሰት ነው::ስብሰባ ለማድረግ አስቀድመው ጠይቀው ከ7/2/67 እስከ22/2/67 ለስራአጦች ተናገን ከሻ/በቀለ ተክሉ፡የወንጀል መከላከል ምርመራ/ እና አዛዥ ፈቃድ ተሰጥቶአቸዋል:: ታዲያ ይህ ሁሉ እውቅ ሆኖ ሳለ የከርታታ ደሃችን ደም ያፈሰሱ፡የስምንቶቹን እብት እንደወጣ ያስቀረው "የምርጦች" መንግስት እንዴት ይዋሻል?

ለጠቅላላው ሕዝብ ደህንነት የመጡ አስመስለው በወታደራዊው ደርግ ስም የሰፊውን ሕዝብ የላብና የደም ውጤት የቀሙት ጥቂት አወናባጅ መኮንኖች ስልጣንን በእጃቸው ካገቡበት ጊዜ ጀምሮ. ብዙ ፋሽስታዊ ድርጊቶችን ፈጽመዋል:: ሃይለስላሴንና የብዝበዛ ጓደኞቹን አወረድንላችሁ እያሉ የሚደነፉብን "ምርጦች" በሰራተኛው፡በገበሬው፡በስራአጡ፡በተራማጅ ወታደርና በጠቅላላውም በሰፊው ሕዝብ ላይ የፈፀሙት በደል ተዘርዝሮ አያልቅም:: "ያለምንም ደም" እያሉ ቢጨፍሩ፡የመሳፍንትና የመኳንንት ደም እንዳይፈሰስ ትልቅ ጥንቃቄ ቢያደርጉም በገጠርና በከተማ ብዙ የድሃ ደም አፍስሰዋል፣ የጠቅላላውን ሕዝብ መሰረታዊ መብቶች ገፍፈዋል፣ "መሬት ላራሹ" ብለው የተነሱትን ጭሰኞች አስረዋል፡በጥይት ቆልተዋል፣ የሰራተኛውን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ መፍጨርጨር የጀመረውን

የሰራተኞች አንድነት ማህበርን አፍክመዋል፤ ተራማጅ ወታደሮችን፥ተማሪዎችንና ምሁራንን አስረዋል፤ አፍነዋል፤ደብድበዋል፤ ረሽነዋል:: እነዚህ ለሲአይኤ የተሸጡ አወናባጅ መኮንኖች ተራማጅ ወታደር ከመደብ ወንድሞቹ ጋር አብሮ በሕዝብ ጠላቶች ላይ የመዘዘውን ሰይፍ ወደሰፊው ሕዝብ እንዲያዞር በመገፋፋትና በማስገደድ ላይ ናቸው:: የጥቅምት 16ቱ ደም ማፍሰስ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው:: በዘመቻው ሳቢያ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን ላይ የሚወሰደው እርምጃም ፋሽስታዊ ነው::

የእነዚህ ከርታታ ኢትዮጵያውያን ንፁህ ደም ደመከልብ ሆኖ አይቀርም:: ሰፊው ሕዝብ ፋሽስቶቹን በሃላፊነት የሚጠይቅበት ጊዜ ሩቅ አይደለም:: ሰርተው እንዳይበሉ ስራ የተነፈጉት፥ በፋሽስት ጥይት ህይወታቸውን ያጡት ወንድሞቻችን ደም ትግላችንን ይበልጥ ያጠነክረዋል እንጂ አያዳክመውም:: ጠቋሚዎቹ በሙሉ እስከተደመሰሱና የሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች በሙሉ እስኪፈፀሙ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል::

ዋስራአጦችና የሰፊው ሕዝብ ትግል ይቀደም
ስራ ወደሰራው፥ስልጣን ወደሕዝቡ ይመለስ::

=========

## የፌዝ ዲሞክራሲ

ትርኢት 1.

ሰፊው ሕዝብ: መሬት ላራሹ፥ስራ ለስራአጡ፥ ተገቢ ዋጋና ዋስትና ለሰራተኛው፥ትምህርት ጤና የኑሮ ዋስትና ዲሞክራሲ ለሁሉ፥ከወታደርና ከሲቪል በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደመደበኛ ቋሚ ሕዝባዊ መንግስት እናምራ፤ ባሁኑ ጊዜ አፋጣጠው የያዙን ችግሮች መፍትሄዎች እነዚህ ናቸው::

የደርጉ 'ምርጦች' ቀሣስና ሲአይኤ አንድነት ሆነው ይመካከራሉ፤ የሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች ግራ ያጋቡአቸዋል፤ ብዙ ያሳስቡአቸዋል፤ አጤ ቀሪጥን አስጠርተው በእርሱ ታዛቢነት ከቀሩት ሁለቱ ወገኖች ጋር እንደሚከተለው ይወያያሉ::

ቀሣስ: የአገር ጉዳይ፥የሕዝብ ጉዳይ ቀላል ነገር እንዳይደለ ተገነዘባችሁት? እኔ ይህን ያህል ጊዜ እንዴት አጋርኩ፥በእንዴት ያለ ዘዴ በእጄ ውስጥ ጠብቤ ይዤው እንደኖ፥ የሁ ትንሽ ባብራራላችሁ ይረዳችሁ ይሆናል:: ግን ለእኔስ ምን አስባችሁልኛል?

'ምርጦቹ': የእርስዎ የስልጣን ጉዳይ አክትሟል፤ በዚህ እድሜ የልጅ ስራ ለመስራት ካልሆነ በስተቀር ለምንም አይጠቅምም:: የስልጣንዎ ጉዳይ አብቅቷል፥አልቋል፤ በዚህ በኩል ምንም ተስፋ አያድርጉ፤ ሰፊው ሕዝብ እንቅር ተፍቶዋታል:: የዘረፉትን ወደ 15 ቢልዮን ብር የሚሆን ገንዘብ ቢመልሱልን ግን ውጭ አገር ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ የፈለጉበት ስፍራ ይህችን የቀረችዎትን እድሜ በደህና እንዲገፉ እናደርግ ልዎታለን፤ ይምከሩበት፥ያስቡበት::

ሲአይኤ: ጃንሆይ፥የእርስዎ ነገር አልቀለለ፤ ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሊበጡ የሚችሉት ል ጋሎት በጣም ቀንሷል፤ አሁን የእርስዎ ስልጣን ላይ መቆየት ለእኛ ምንም ጥቅም አይሰጠንም:: በእርስዎ መልካም ፈቃድ ደህና ደህና ቡችሎች አሳድገናል፤ በእነርሱ አማካይነት ጥቅማችንን የበለጠ ለማስጠበቅ እንችላለን:: ለውለታዎ አደጋ እንዳይደርስብዎ እናደርጋለን:: 'ከምርጦቹ' ጋር ተግባብተው የስልጣን ላይ መቆየት መቻል

ለምድያን ቢያስረዱና ከወሰዱትም ገንዘብ ግማሹን እንኳን በመልሱ ወደአሜሪካ ሄደው እንዲጠሩ ልናደርግ ያ እንችል ይሆናል፡ ያሰቡበት፡፡

ቀሃስ — መልካም፡ጥሩ፡ጉዳዩ ገብቶኛል፡፡ ገንዘብ መከጀላችሁ ከንቱ ነው፡ምንም አልሰጣች-ሁም፡፡ የእኔ ፍቅረንዋይ ምን ያህል እንደሆነ ሳታውቁ ቀርታችሁ ነው ይህን የም ተጠይቁኝ? አስደንቆኛል፡፡ገንዘብ፡ብዙ ገንዘብ ለኛ ሁልጊዜ ያስፈልገናል፤ እወቁት፡፡ ስልጣን ላይ የመቆየቱ ዘዴ ሚኪያቬሊን ደህና አድርጎ ማሳመጥ ነው፤ አስተዋይነት ብልህነት ትእግስት ወዘተ. የመሳሰሉትን ከከፋፍለህ ግዛ ጋር ማጠመርና ማዋሃድ ነው፡፡ የዜና ማሰራጫ መሳሪያዎቻችን በሞኖፖል ይዛችሁ በሬ ጥጃ ወለደ፡ገደሉ ሜዳ ነው፤ ሕዝባዊ መንግስት፡ዲሞክራሲ ወዘተ. የሚሉት የመሳፍንትና የመኳንንት ቅሬቶች የውጭ እጅ፡ የጠላት መሳሪያ ወዘተ. ናቸው እያላችሁ የፕሮፓጋንዳ ቀልቀሎቻችሁን መከፈት ነው፤ በሃይል ንፋት፡፡ይህ ብቻ ጥቂት ጊዜ ሊያስነብታችሁ ይችል ይሆናል፡፡

ሲአይኤ — ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ኝንሀይ ያደረጉ እንደነበረው እነዚህን ሕዝባዊ መንግስት፡ ዲሞክራሲ ወዘተ. እያሉ የሚጮሁትን ተማሪዎች፡ሰራተኞች፡ምሁራንና ሌሎችንም የሰፊውን ሕዝብ ክፍሎች በሃይል መምታት አለባችሁ፤ ለመሳሪያው እኛ አለን፤ ሌላም እርዳታ ይሰጣችሗል፤ ለአጤ እንሰጥ ከነበረው አስበልጠን እናቀርብላችሗለን፡፡ ምክራችንን ከተከተላችሁ፡ትእዛዛችንን ከፈፀማችሁ በሌላው በኩል ከቶ አሳብ አይገባችሁ፤ እስከ መጨረሻው ድረስ ከእናንተው ጋር ነን፡፡ በቪየትናምና በሌሎችም አገሮች ያደረግነውን ታውቁ የለም? ብቻ ይህ ምስጢር ነው፤ ሰፊው ሕዝብ እንዳያውቀው ተጠንቀቁ፤ የእኛ ስም እንዳይነሳ፡፡እኛ እንኳን ሌላ አለን፤ ይብላኝ ለእናንተ እንጅ የአጤና የፍጡሮቻቸው እድል ለሚጠብቃችሁ፡፡

'ምርጦቹ' — ሁለታችሁንም ከልባችን እናመሰግናለን፤ ቀሪጥ ምስክራችን ነው፡፡ የገንዘቡ ጉዳይ በሰፊው በሕዝብ ዘንድ ከመሰማቱም በላይ ቀደም ብሎ በደንብ የታወቀ ስለሆነ ኝን ሀይ አሁን አንለቅያትም፤ 4ኛ ክፍለጦር ወስደን ደንበኛ ሺሳ ውስጥ እናስቀምጥያታለን፤ ገንዘቡን አለመልስ አሉን እያልን ሰፊውን ሕዝብ ለጥቂት ጊዜ እናወናብድበታለን፡፡

ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲ፡ሕዝባዊ መንግስት፡ከወታደርና ከሲቪል በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አሁኑኑ ይቋቋም ከማለት ወጥሮ ያዘን፤ ሲአይኤ፡ምን ይሻላል. ምን እናድርግ. በሃይል ተቸገርናል፡፡

ሲአይኤ — አበዳችሗል እንዴ? የምን ሕዝባዊ መንግስት ነው? ዲሞክራሲ ለእኛ እንጂ ለእናንተ አይሆንም፤ እዚህ ቦታ የለውም፡፡ አሳባችንን በትክክል የተረዳችሁት አይመስለንም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚያስፈልገው ጠንካራ መንግስት ነው፡፡ ጠንካራ መንግስት ደግሞ የወታደር መንግስት ነው፤ የእኛ ቢችላ ማለት ነው፡፡ በእኛ ምርጥ ኤክስ TC ቶችና በእናንተ 'ሊቃውንቶች' ተጠንቶ አልቋል፡፡ ዋናው ተግባራችሁ ይህን ስራ ላይ ማዋል ብቻ ነው፡፡ የታወቁት አባሎታችን እነዲጎፖል፡እነክሪና ሌሎችም ወደዚህ መጥተው ስራቸውን ከጀመሩ ሰንበተዋል፡፡ እነርሱ የሚሉአችሁን ዝም ብላችሁ መቀበልና መከተል ነው፤ እንደምታውቁት ኢትዮጵያን ከእናንተ ይባልጥ ያውቃሉ፡፡ ለዚሁ ለእናንተ ጉዳይ ከእነርሱ የተሻለ የለምና የሚሉአችሁን አጥብቃችሁ መከተል

ብቻ ነው፡፡ ስለበለዚያ ምን ሊደርስባችሁ እንደሚችል ታውቀ የለም? ስያን ቀልድ
የለም፤ የተዘጋጀው የወታደር መንግስት ቶሎ ብሎ ይታወጅ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ
ንን ከፍ ያለ የኢኮኖሚና የስትራተጂ ጥቅም ለመጠበቅ የሚችል የወታደር መንግስት
ብቻ ነው፡፡ የዴሞክራሲን ጉዳይ ለጊዜው ለአሜሪካና ለአውሮፓ ማለት ለነጮች ተውት፡፡

ትርኢት 2.

•ምርጦቹ• የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀይ ደስ ይበልህ! በዛሬው ቀን አጤ ሃይለስላሴን ከስልጣን
አውርደን አስረናል፤ አልጋወራሹ መጥተው ዘውዱ እስኪጭኑ ድረስ ጊዜያዊ ወታደራዊ
መንግስት አቋቁመንልሃል፤ ባለህበት እርጋ፤ ለጥሰጥ ብለህ ተገዛ፡፡ የሚያንገራ
ግርና የሚበጠብጥ ይቀጣል፤ ሰአት እላፊ ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል እስከጥዋቱ
አስራሁለት ሰአት ነው፡፡ የጦር ሃይሎችና ፖሊሶች አዋጁን እንዲያስከብሩ ታዘዋል፤
ተባረኩ፡አሜን፡፡

ሰፊው ሕዝብ ጨቋኙና ግፈኛው አጤ ሃይለስላሴ ከስልጣን መወገዳቸውን በደስታ ተቀብለነዋል፤
የሰላማዊው ሕዝብና የጦር ሃይሉ የትግል እንቅስቃሴ ውጤት ነው፡፡ ሆኖም ሶስት
ተቃውሞዎች አሉን፡፡ አንደኛ፡የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ መታወጅ ሲገባው ዘውዱ ይቀጥላል
ማለቱን በጥብቅ እንቃወማለን፤ ሁለተኛ፡ከወታደሩና ከሰላማዊው ሕዝብ በምርጫ የተ
ውጣጣ የሕዝብ መንግስት መቋቋም ሲገባው የወታደር መንግስት ለብቻው መቋቋሙን
በሃይል እንቃወማለን፤ ሶስተኛ፡መሰረታዊ መብቶቻችን ተከብረውና ተጠብቀው ትልቅ
የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ ሲገባን መብቶቻችን በግልጽ መገፈፋቸውን አጥብቀን እን
ቃወማለን፡፡እነዚህ አሁኑኑ ካልተለወጡና በጥያቄያችን መሰረት ካልተፈፀመ ትግላችን
አይፈታም፤ ይቀጥላል፡፡

•ምርጦቹ• እኛ ስልጣን አንፈልግም፤ በአፍንጫችን ይውጣ፤ ገብርኤልን፡ሚካኤልን፡ማርያምን፤
ስልጣን ብንፈልግ ኖሮ እስካሁን ድረስ ማን እጃችንን ያዘን? ይህን የሚያስወሩ
አንዳንድ ተንኮለኞች ናቸው፡፡

ሰፊው ሕዝብ ሲአይኤ የሚባለውን ጭራቅ ታውቃላችሁ? ቡችሎቹ በዙሪያችሁና በውስጣችሁ ጭምር
መኖራቸውን የምትክዱ ከሆነ ስለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ያላችሁን አቋም በግሃድ
ግለጡ እስቲ? ሰሞኑን ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የጦር መሳሪያ ከአሜሪ
ካን ኢምፔሪያሊዝም በመቀበል ላይ መሆናችሁ አልተገለጠም? ታዲያስ ምን ልታደርጉ
በት ነው? ለውጭ ጠላት ወይስ እኛን ለመጨፍጨፊያ? ምኞችሁን ፈልጉ፤ እናንተ
ቤት ያደረው ብልጠት እኛም ዘንድ አምሽቶአል፡፡

ሲአይኤ ታዲያስ ጉበዝ! ነገሩ አልቀለል፤ መጋረጃው ተገልጦአል፤ ምስጢራችን ታውቆአል፤
እኛም እናንተም ተጋልጠናል፡፡ የፕሮፓጋንዳ ወናፋችሁን ደህና አድርጋችሁ ወልውሉ፡
አጠናክሩ፤ አጫፋሪያች መልምሉ፡ቁጥራቸውን በርከት አድርጉ፤ ገንዘብ በተኑላቸው፤
የኢኮኖሚ ችግር ቢኖርብንም ለዚህ ያህል አይገድም፤ ወደዋሽንግተን አስቸኳይ ቴሌ
ግራም አስተላልፈናል፤ ሁሉም ነገር ይመጣላችሃል፤ ፍፁም አትስጉ፤ ጦሩንም በደ
ንብ አስታጥቁት፡፡ ከዚያም 'ሕዝባዊ መንግስት'፡ዴሞክራሲ እያሉ የሚጮሁትን አጤ

በተካኑት በከፋፍለህ ግዛ ዘዴ በመጠቀም ቶሎ ብላችሁ አድክሙአቸው::እስከአሁን ድረስ ደም አላፈሰስንም፣ ለውጡ ያለደም መጣ ያላችሁትን ለጊዜው ወደጉን ተውትና ሰላማዊውን ሕዝብም ሆነ ወታደሩን ለመምታትና ደሙንም እንደጉርፍ ለማፍሰስ መዘጋጀት ይኖርባችኋል::

በዚህ ትእዛዝ መሰረት አንድ ሻለቃ ጦር ከሃረር ይመጣና የምድር ጦር መሃንዲስን በድንገት ይመታዋል:: 5 ሰዎች ወዲያው ይሞታሉ፣ 6 ቆስለው ወደሆስፒታል ይወሰዳሉ፣ ሰፈሩ ይያዛል፣ አባሎቹ በሙሉ ይታሰራሉ::የምድር ጦር አየር ክፍል/አርሚአቪሽን/ አባሎችም ይታሰራሉ::ከክብር ዘበኛ:ከአየር ሃይልና ከሌሎችም ክፍሎች የሕዝብ ወገን የሆኑት ግንባር ቀደሞች ይታሰራሉ:: ተማሪዎች:ሰራተኞች:ጭሰኛና ድሃ ገበሬዎች:ምሁራን ተራማጆች ይደበደባሉ፣ ይታሰራሉ፣ አንዳንዶቹ ከቀድሞዎቹ ጨቋኞችና በዝባዦች ጋር ባንድነት 4ኛ ክፍለጦር ውስጥ ይታጉራሉ:: ግን ይህ ሁሉ ትግሉን አያበርደውም፣ ይበልጡኑ እየተፋፋመና እየጠነከረ ይሄዳል::

ትርኢት 3.

ሰፊው ሕዝብ — ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረግ፣ ከሲቪልና ከወታደር በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግስት ቶሎ ይቋቋም፣ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን መንግስት አንፈልግም፣ ኢምፔሪያሊዝም:ፋሽዝምና ፊውዳሊዝም ይውደሙ፣ የንግግርና የጽሁፍ: የማህበርና የሰላማዊ ሰልፍ መብቶች ለዘላለም ይኑሩ::

•ምርጦቹ• — ዲሞክራሲ:ዲሞክራሲ እያሉ መጮህ ምን ትርጉም አለው. ሰፊው ሕዝብ እኮ አልነቃም: አልተደራጀም:: ተማሪና ምሁር:"እድገት በህብረት:የእውቀትና የስራ ዘመቻ" የሚባል ፕሮግራም ተዘጋጅቶአልና ወደዚያ ሄዳችሁ ገጠሬውን ሕዝብ አስተምሩ፣ አይኑን ግለጡለት:: ይኸን የማይቀበል የሕዝብ ጠላት ነው፣ የንጉሳውያን:የመሳፍንት:የመኳንንት:የተያዙት ባለስልጣኖች ርዝራዥና ቀሪት ነው::

ቀልቀሎች /በአሉ ግርማ: ጳውሎስ ኞኞ: አጥናፍሰገድ ይልማ:አለማየሁ ሞገስ: ወዘተ./ — አዎን አዎን፣ ዲሞክራሲ:ሕዝባዊ መንግስት ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም፣ ይህን የሚፈልጉ የቀድሞ መንግስት ደጋፊዎች:የመሳፍንት የመኳንንት የተያዙት ባለስልጣኖች ልጆችና ዘመዶች ናቸው:: ደግሞስ ዲሞክራሲን ምኑን አውቀውት? የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንና አስተማሪዎቻቸውን ብንወስድ ለ8000 የዩኒቨርሲቲ ሰው 4000 የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚመርጡ:ለዲሞክራሲ ያልደረሱ:ያልበሰሉ ናቸው:: የቀረው ሕዝብማ ዲሞክራሲን ምኑን አውቆት? ምንስ ሊያደርግለት? ፋሽስት ወታደራዊ መንግስት:ሲአይኤና ኢምፔሪያሊዝም ለዘላለም ይኑሩ! እኛንም ከገንዘቡ ከሹመቱ በሉን:አትርሱን፣ ሞግዚታችን:አለቃችን ሲአይኤ ያዘዘልንን አታስቀሩብን፣ በርትተን እንተባበር፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጥቅም እንዲጠበቅና እንዲስፋፋ ማድረግ ዋናው ተግባራችን ነው፣ አሜን::

ሰፊው ሕዝብ — ችግሮቻችን ትክክለኛውን መፍትሄ ማግኘት የሚችሉት በዲሞክራሲ ነው፣ ሕዝባዊ መንግስት ስንል ጨቋኞችና በዝባዦች የማይሳተፉበት የሰፊው ሕዝብ መንግስት ማለታችን ነው:: በጨቋኞችና በበዝባዦች ነፃነት ላይ ገደብ ይደረግበታል፣ ቀንደኞቹ:በሕዝብ ላይ ግፍ የሰሩት:የተያዙትና ገና ያልተያዙት ሁሉ በፍጥነት ተይዘው:ሁሉም ወደልዩ

የፍርድ ሸንጐ ቀርበው ያለምንም ይግባኝ ቀጣታቸውን እንዲቀበሉ ይደረጋል:: ታዲያ የእኛ ጥያቄ ይህ ሲሆን 'የቀደምያቹ ባለስልጣኖች ርዝራዦና ቀሪት ናችሁ፣ እነርሱን ለማስፈታት ነው ሕዝባዊ መንግስት:ዲሞክራሲ እያላችሁ የምትጮሁት..' በማለት ስማችንን የምታጠፉት ለምንድነው? የሕዝብ እንጡራ ገንዘብ የሆነውን የዜና ማሰራጫ መሳሪያ በሞኖፖል ይዛችሁ የማርከስ የማቆሸሽ የማጥላላት የፕሮፓጋንዳ ወናፋችሁን በመለቀቅ የምታሸንፉ ይመስላችሁ ሂል? ድካማችሁ ከንቱ ነው፣ በመጨረሻ ድሉ የኛ ነው:: አይናችሁን ከፍታችሁ ታሪክን ለመመልከት ብትሞክሩ ከብዙ አደጋ ለመዳን ትችሉ ይሆናል::

**!ምርጦቹ**

አዋጅ!አዋጅ! የዲሞክራሲ አዋጅ:'የመማክርት ኮሚቴ አባሎች'በ15 ቀን ውስጥ ወርጣችሁ እንድትልኩ፣ ሰዎቹ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው: የኢትዮጵያ ትቅደምን /ምርጦቹና ኢምፔሪያሊዝም ይቀደሙ/ ፍልስፍና ደህና አድርጐ የሚያውቅ፣ ችሎታ ያለው:የተማረ/ማን ይሆን የሚለካው/፣ በሕዝብ ላይ ገፍ ያልሰራ፣ መጥፎ ጠባይና ልማድ የሌለበት/የማይሰክር የማያመነዝር ወዘተ./:: 23 ሚልዮን የሚሆነው 'አይኑን ያልከፈተ'ጭሰኛና ድሃ ገበሬ አንድም ወኪል አይመርጥም:: ለ15 አመታት ያህል ደሙን በማፍሰስ:ህይወቱን በመሰዋት ጨቋኙንና በዘባዡን የሃይለስላሴን መንግስት ሲቋቋም የቆየው ተማሪም ምንም ወኪል አይኖረውም፣ በሚልዮን የሚቆጠረውም የሰራ አጥ ሰራዊት እንደዚሁ:: ግማሽ ሚልዮን የሚሆነው ሰራተኛ 3 ወኪሎች ይመርጣል:: ወደ20 ሺ የሚሆኑ መምህራን/ድጋፍ ሰጥተውናልና/ 6 ወኪሎች ይኖራቸዋል:: እንዲሁም ከየመስሪያ ቤቱና ከየክፍለ ሃገሩ ቢሮክራቶች ይመረጣሉ:: ይኸ አይደለም ዲሞክራሲ ማለት?

የመረጣችኋቸው ወኪሎቻችሁ ስራም ለእኛ ሃሳብ ማቅረብ ነው፣ ብንፈልግ እንጠቀምበታለን፣ ካላስደሰተን ደግሞ ቀዳድደን ቆሻሻ ወረቀት መጣያ ውስጥ እንደለዋለን::

**ቀለ ቀሎች**

ታዲያስ:ዲሞክራሲ ባዮች:አልኩባዮች:ይኸውላችሁ! እንግዲህ ምን ናራችሁ! ስትጮሁለት የነበረውን አገኛችሁ አይደለም? በሸዋ ክፍለ ሃገር የበላይ ሹማምንት ተሰብስበው ምክትል አስተዳዳሪውን መረጡ፣ ከሃረር ቀኛ/ይጥና አበበ በ74 ድምጽ ተመረጡ:: የጐጃም ሕዝብ ክቡር አቶ ሃዲስ አለማየሁን:የወሎ ሕዝብ ክቡር አቶ አሰፋ ሊበን: የአሩሲ ሕዝብ ደክተር ጥቀሄር ሃይሉን ወዘተ. መረጡ::

**ሰፊው ሕዝብ**

የንግድ ሚኒስቴር ሰራተኞች ከአምስት የማያንስ ጊዜ ተሰብስበው አናምንበትም:አንመርጥም ብለው በመጨረሻ አፍኝ የማይምሉ አድርባዮች ከመካከላቸው እንዳን መርጠዋል:: የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴርም እንደዚሁ:: ይህ ዲሞክራሲ አይደለም:ቀልድ ነው:: በዚህ አይነት መንገድ ተመርጦ የሚላከው ተላላኪ እንጂ ደንበኛ ስልጣን ያለው ወኪል አይደለም::ገሩም ዲሞክራሲ! አጡብ ድንቅ ነው::በዲሞክራሲ ከገሪክችም ሳንበልጥ አይቀርንም:: በመንግስት ለውጥ:በሬቮሉሽን አለምን ማስተማር እንደጀመርን አሁን ደግሞ ዲሞክራሲ ምን እንደሆነና እንዴት ስራ ላይ እንደሚውል ለመላው አለም አብነት መሆናችን ነዋ! እኛ ግን ትግላችንን ከመቀጠል በዚህ ርካሽ ማጭበርበር አንረታም::

'ምርጫ'

'...የጦር ኃይል አባሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍፁም የሆነ የሰቫል የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነፃነት ለመስጠት ቃልኪዳን ገብተዋል:: ይህ የማይታጠፍ ቃላችን ነው:: ግን አስቀድሞ ስይኑን እንዲከፍት/አውር ነውን?/ የፖለቲካ ን...ት: የአስተሳሰብ ለውጥ አግኝቶ የራሱ እድል ወሳኝ እንዲሆን ማድረግ ነው::' ለዚሁም የአውቀትና የስራ ዘመቻ አዘጋጅተናል:: ይህ አስኪከናወን ባለንበት መቆየት አለብን:: እና ከላይ ፈላጭቆራጭ በንህንም አናንተ ሃሳብ አቀራቢ ተላላኪ እንድትሆኑ ይፈቀድላችሃል፣ በደ...ዝና በአበል ግን አትበደሉም፣ ቢያንስ ቢያንስ ፀረዲሞክራሲ በሆነ መንገድ ይመረጡ የነበረትን የፓርላማ አባሎች ያህል ባታገኙ አትቀሩም:: ሕዝቡ የጣለባችሁ አደራና ሃላፊነት ከባድ መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም:: ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመርጣችሁ የመጣችሁ የ26 ሚልዮን ተኩል ሕዝብ ወኪሎች ናችሁና! ተገባብተናል አይደለም? ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ ነው:: ፍሬ ነገሩ ይህ ነው::

ቶሎ ቶሎች

የሕዝብ ሸንጎ ተሰበሰበ፣ የደርጉ ሊቀመንበር በሰፊው ሕዝብ ልዩልዩ ክፍሎች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመርጠው የተላኩትን ከአርባ በላይ የሚሆኑ የሕዝብ እንደራሴዎች ተቀብለው አነጋገሩ፣ ስለስራቸው መምሪያ ሰጡአቸው፣ ሕዝቡ ከባድ ሃላፊነት የጣለባቸው እንደሆኑ መጠን በሁኑ የመሸጋገሪያ ወቀት ከደርጉ ጋር ተለቅ የስራ ድርሻ እንደሚሮባቸው ገለጻ አደረጉላቸው:: ከሊቀመንበሩ ንግግር በኋላ አቶ እንተኔ በ...ክፍለሃገር ተወክለው የመጣት 'የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች የፖሊስ ...ራዊትና የብሄራዊ ጦርሰራዊቶች ጨቋኙን የመሳፍንትና የመኳንንት መንግስት ከሕዝቡ ጫንቃ ላይ አሽቀንጥረው በመጣል ፍፁም ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መስርተው እኛ የመጀመሪያ ወኪሎች ሆነን እንድናገለግል በመደረጉ ታላቅ ክብር ስለተሰጠኝ ክቡር ሊቀመንበሩን ከልብ አመሰግናለሁ' በማለት ልባዊ የሆነ ደስታቸውን ገልጠው የመታሰቢያ ፎቶ ተነስተው የበአሉ ...ፃሜ ሆነ::

ይሸውላችሁ እንግዲህ ሕዝባዊ መንግስት መቋቋሙ አይደለምን? ምን ቀረው? ታላቁ ሸንጎ ስራውን ጀመረ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲመኘው የነበረው ሁሉ ተሟላለት፣ እንግዲህ ሸንጎን ገትሮ መስራት ነው፣ መስራት ነው፣ ዛሬም ነገም ሁልጊዜም ሸንጥን ገትሮ ወገብን ደድቶ 24 ሰአት መስራት ነው:: የሚያዋጣው ስራ ብቻ ነው:: ከእንግዲህ ወዲያ ሕዝባዊ መንግስት: ዲሞክራሲ ማለት የለም፣ ደርጋችንን ዘለአለም ያኑረው፣ ምን ጉድሉ እንግዲህ: ሁሉ በጃችን ሁሉ በደጃችን::

ሰፊው ሕዝብ

ዲሞክራሲ. ሕዝባዊ መንግስት. መሰረታዊ ሰባዊ መብቶችና ነፃነቶች በቃልይ የሚታለፉ አይደሉም፣ አሁኑኑ ስራ ላይ መዋል አለባቸው:: መሬት ላራሹ: ለስራአጡ ስራ: ትምህርት ለሁሉ: ለሰራተኛው ተገቢ ዋጋና ዋስትና: ጧሪ ለሌላቸው ጡረታ: የጤና አገልግሎት ለሁሉ: በድርቅና በችጋር ለሚሰቃዩ አስቸኳይና በቂ እርዳታ ይደረግ፣ ችግራችን ባሰ እንጂ ምንም አይነት መሻሻል አላየንም:: ከአሮ ዘሎ ቀዘን እንዳይሆን ያሰጋል:: ትግላችን ድሉን እስከመጨረሻ ድረስ ይቀጥላል፣ ምንም ሃይል ሊያቆመው አይችልም::

## ዲሞክራሲ በአጤ ሃይለሰላሴና 'ምርጦቹ' አይን

### ቀሃስ

'..በነዚህም የምክር ቤቶች የሚመከሩ አማካሪያች: ሕዝቡ ተምሮና አውቆ ለመምረጥ እስኪችል ድረስ በንጉስ ነገስቱ ፈቃድ ከያውራጃው እየተመረጡ ይመጣሉ::' .....1923

'..ከዚህም ወዲያ የሕዝባችን እውቀቱ የበቃ በሆነ ጊዜ ለዚህ ምክር ቤት የሚሆኑን አማካሪያች ራሱን ችሎ እየመረጠ ሊሰድልን ይቻላል..' 14/11.'24

'..የተወደደውን ሕዝባችንን መርተን አሰልፈን በስልጣኔ ደረጃ ተደርሶበት የማይታወቅ እርምጃ ወደተገኘበት ዘመን ስለአደረስ ነው...' 24/2/48

'ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን የአገራችንን የደረጀ ቀርስ መሰረት በማድረግ የሕዝባችንን የወደፊት እድል ለማሻሻል የጀመርነውን ታላቅ የስራ ትግል ከግቡ ለማድረስ እናንተም የፓርላማ አባሎች ከፍ ያለ ድካም ይጠብቃችሗል::' ...23/2/51

### 'ምርጦቹ'

'..ሰፊው ሕዝብ አይኑን እስኪከፍትና የፖለቲካ ንቃት..አግኝቶ የራሱ እድል ወሳኝ እስኪሆን ድረስ..'ጠንካራ ወታደራዊ መንግስት ያስፈልገዋል:: ....መስከረም 1967

'..'እውነተኛዋን ነፃነት ትርጉምና ጥቅም በጥሞናና በዘዴ ማስረዳት ተገቢ መሆኑን እናምንበታለን፣...ግቡንም ፈፀምኩ ብሎ ልቡ የሚያርፈው የሕዝቡን ሙሉ ነፃነት በተስተካከለ መንገድ ሲያስጠብቅ ብቻ ነው::' ....25/1/67

'በቁጥር በጣም አነስተኛ የሆነው የተደራጀውና በፖለቲካ የነቃው ክፍል ብቻ እንደጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድል ወሳኝ ተቆጥሮ መሰው የአገሪቱ ሕዝብ ሳይረዳውና ሳያምንበት የጥቂቶቹን ፍላጐት ብቻ የሚያረካ እርምጃ መውሰድ ከአለፈው የተመሰቃቀለ የአስተዳደር ፈሊጥ የማይሻል...'ነው::

'..የሰፊውን ሕዝብ ለለውጥ መዘጋጀት እጅግ አስፈላጊነት አጥብቀን ተረድተነዋል::' ....1_/1/67

ብዙ ተመሳሳይ ጥቅሶች ለማቅረብ ይቻላል፣ የበፊቱና የአሁኑ ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው፣ አብዛኞቹ ሰዎችም/ባለስልጣኖችም/ ቢሆኑ ያው አንድ ናቸው፣ የሃይለስላሴ ፍጡሮች: የመሳፍንቱ የመኳንንቱ ዘመድ አዝማዶች: የባለስልጣኖቹ ግብረአበሮች ዛሬም እዚያው ናቸው:: አንዳንዶቹማ ከባድ ስልጣን ጨብጠዋል:: በእውነት ስለእውነት ብለን እንናገርና እነዚህ ሰዎች ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅም ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ ወይ. 'ምርጦቹ' ዙፋን ላይ ከወጡ ወዲህ የሰፊው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ምን ያህል ተለወጠ. ለውጥ ቢኖር ብዙ ሰው ከስራ መባረሩና የስራአጡ ሰራዊት በእጥፍ ማደጉ: ተማሪው ከትምህርቱ መቋረጡ: አብዛኛው ገጠሬ በረሃብ ማለቁ: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው ተዳክሞ የነበረው ኤኮኖሚ እንኩትኩቱ መውጣቱና አገሪትዋ የመጨረሻዋ ምስኪን መሆንዋ ነው:: የሰፊው ሕዝብ እንጡራ ሃብት ግን የሕዝብ ወገኖችን ለማደንና ለማሰቃየት ለአሜሪካን ከርካሳ ጅኘና እንዲሁም 'ለምርጦቹ' ለአድርባዮች የቀን አበል ይፈሰሳል:: ሰፊው ሕዝብ በደለኞቹን የሚፋረድበት ጊዜ እሩቅ አይደለም::

እውነተኛው ዲሞክራሲ ያሸንፋል
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::

# የትግል ዜናዎች

## የገብረየስ ቤኛና የአሸቱ ወልደፃድቅ መለቀቅ:—

'ደርጉን ተቃወማችሁ: ትእዛዙን ጣሳችሁ: ከህግ ውጭ ተሰበሰባችሁ ወዘተ.' በመባል ብዙ ሰራተኞች ደሞዛቸው እንደጐርፍ ሲፈስስ: ተራማጆችና ተማሪዎች ሲደበደቡ ሲታሰሩና ከቀድሞ ጨቋኞች ጋር በጨለማ ቤት ውስጥ ሲታጐሩ: ሁለት ቀንዳም ዘራፊዎችና አጭበርባሪዎች ባለፈው ሳምንት በነፃ ተለቀቁ::

የአማልጋሜትድ ኩባንያ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ: ገብረየስ ቤኛ ከቀድሞ ባለስልጣኖች ጋር በመሻረክና በመመሳጠር የሰፊውን ሕዝብ አንጡራ ሃብት ሲገፍፍ ቆይቶአል:: ገብረየስ ቤኛ ከቀድሞው ልማት ባንክ ዋና ስራ አስኪያጅ ከአሰፋ ደምሴና ከሌሎቹም መሰሎቹ ጋር በነበረው የጥቅም መመሳጠር ባለፈው አመት ማዳበሪያ ለማስመጣት ካደረገው ውል ውጭ አንድ ሚልዮን ብር ያህል የዘረፈ መሆኑ የይፋ ምስጢር ነው:: ገብረየስ ቤኛ ለጥቂት ቀናት ያህል ተይዞ ያለምንም ቅጣት የቀድሞ ስራውን ጀምሮአል:: ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በአሩሲ ክፍለአገር ለብዙ አመታት የዳራ ማዘጋጃ ቤት ሹም የነበረው ትልቁ ገበሬ አሸቱ ወልደፃድቅ የጭሰኞችና የድሃ ገበሬዎች ጠላት መሆኑ የታወቀ ነው:: በዛሬው ጊዜ 46 ጋሻ መሬት ለብቻው ይዞ የሚያርሰው ባንድ በኩል የመንግስት ሰራተኛ በሌላ በኩል ዲታ ገበሬ ስራ ከጀመረ አንስቶ ጠቅላላ ደሞዙ ከ46 ሺ ብር የማይበልጠው በአሁኑ ጊዜ በአሁኑ ጊዜ ከሁለት ሚልዮን ብር በላይ የሚያወጣ ሃብት አከማችቶአል:: የዚህ ዘራፊና ፀረጭሰኛ መለቀቅ የሚያስገርም ነው::

## የሰፊው ሕዝብ ትግል በመስፋፋት ላይ ነው:—

የሰፊው ሕዝብ ትግል በገጠሩ በመስፋፋትና ስር በመስደድ ላይ ነው፤ በኤርትራ በትግራይ በሃረር በሲዳሞ በባሌ በበጌምድር በጐጃምና በሌሎችም ክፍለሃገሮች በመፋፋም ላይ ነው:: በከንባታ በወላሞ በሲዳማ በደራሳ በጨርጨር በሃብሮ በሰላሌ ወዘተ. ጭሰኞችና ድሃ ገበሬዎች ከባለብዙ መሬት ነፍጠኞችና ባላባቶች ጋር እየተጋጩ ናቸው:: 'የምርጦቹ' መንግስት ወታደርና ፈጥኖደራሽ ልኮ ሃብታሞቹን በማገዝ ሰፊውን ሕዝብ ደብድቦአል:: ብዙ ጭሰኞችና ድሃ ገበሬዎች 'ኢትዮጵያ ትቀደም'ን ተቃወማችሁ ተብለው በሃሰት ምስክር እየተመሰከረባቸው መታሰራቸው ታውቆአል:

## የጅማው ፋሽስታዊ ድርጊት:_


አንድ 'ከባድ ውሃ' የወሰደ የንጉስ ደርግ አባል ባለፉት ቀናት ጅማ ከተማ ውስጥ አንድ ተማሪ በጥይት ገደለ:: በዚህ ሕዝቡ በሃይል ከመቆጣቱም በላይ ድርጊቱ ያስቆጣቸው ተማሪዎች በማወናበጃው ዘመቻ የማይካፈሉ መሆናቸው ይነገራል::


## የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘመቻውን ተቃወሙ:

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች 'የምርጦቹን' ማስፈራራት ከምንም ሳይቆጥሩት በማወናበጃው ዘመቻ የማይሳተፉ መሆናቸውን ከፍ ባለ የድምጽ ብልጫ ወሰኑ:: ተቃውሞአቸው ዘመቻ ጨርሶ አያስፈልግም በማለት ሳይሆን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ሳይቋቋምና የሰፊው ሕዝብ መሰረታዊ መብቶች በስራ ላይ ሳይውሉ ለሰፊው ሕዝብ ጠቃሚ የሆነ ዘመቻ ማድረግ አይቻልም በማለት ነው::

## የጳጳሳት ፍቅረንዋይ:

በከተማው ሕዝብና በተማሪዎች በተደረገው ስብሰባ የክፍለሃገሩ ጳጳስ የሃይማኖት ሃላፊነታቸውን ዘንግተው በአስተዳደር ከመባለጋቸውም በላይ ከፍተኛ የብዝበዛ ተግባር በሕዝቡ ላይ በመፈፀማቸው በሕዝቡ በይፋ ተወቀሱ: ተገሰፁ፤ አቡኑም እንደሚፈርና እንደመፍራት ብለው ከክፍለሃገሩ ከበለለው ጠፍተዋል:: አቡነ ቴዎፍሎስም በተመሳሳይ ወንጀል ባለፈው ቀዳሚ እንዲነሱ ተጠይቀው ነበር::



'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለው ዘይቤ 'አሜሪካ ትቅደም'ከሚለው ፋሸስት አባባል የተቀዳ መሆኑ የታወቀ ነው። በዚህ ስእል እንደሚታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስፈራራት የምትሃት የአስማትና የሟርት መሰል ዘዴ በመጠቀም በኢትዮጵያ ካርታ ላይ ያደርገ ቆብ ደፍቶ የሚያፈጠው አይን ከአሜሪካን አንድ ብር ላይ የተቀዳ ይመስላል። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም ማለቱ የበለጠ ተቀባይነት ኖሮት የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ምልክት ይሆን ነበር።